# ግንቦት ሰባት ድርጅት በተግባር ትግሉን ተቀላቀል።

ከእለኒ አለሙ።

የፍትህና የዲሞክራሲ የነፃነት ትግል ዋጋ ያስከፍላል ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ በአምባገነንነት የተቀመጠው የህዋት ወያኔ ሥርዓት በወረቀት መግለጫና በንግግር ብቻ የሚወገድ ሥርዓት ቢሆን ንሮ እስከ ዛሬ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም ግንቦት ሰባት የሰጠው መግለጫና የድርጅቱ መሪ ዶክተር ብርሃኑ እስከ ዛሪ ያደረጉት ንግግርና ማብራሪያ ከበቂ በላይ ሁኖ አስተዳደሩን ወደማይቀረው መቃብር ይወረውረው ነበር። ይህ አልሆነም። በንግግርና በሰላማዊ ውይይት የትም መድረስ እንደ ማይቻል ቀደሞ ያስተማረውና ፋኖ ተሰማራ በማለት ወደ ኤርትራ በርሀ በመውረድ ከሰባት ዙር በላይ ነፃ አውጭ አደራጅቼ ሠራዊቴን በመላው የሀገሪቱ ክፍል አስማርቻለሁ።ከሰራዊታችን ጋር ለመቀላቀል ኤርትራ በርሀ መምጣት ሳያስፈልግ በየ ጎሮችህ አለን በማለት ኦፍሻላዊ መግለጫ የሰጡን የግንቦት ሰባት ኮማንደር ብርሀኑ ነጋ ነበሩ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ በመነሳት የህዋት ወያኔን ስርአት ለማስወገድ ብረት አንስቶ እየተፋለመ ነው።በኦሮማይ ክልል የተነሳው ንቅናቂ ከልጅ እስከ አዛውንት ያደረገው አመፅ ሥርዓቱን አናግቶታል። እርሰዎ ኮማንደር ብርሀኑ ከሚኖሩበት ኤርትራ ከሶስት ሰዓት የእግር ጉዞ በማይፈጀው የወልቃይት፣የማይጸብረ ፣የሳንጃ፣ የዳንሻ፣የሁመራ፣የማይካድራና አብደራፊ በርሀዎች ጀግናው የጎንደር የአማራ ህዝብ ከህዋት ወያኔ ሠራዊት ጋር እየተናነቀ ነው። የአማራው ሕዝብ ላነሳው የነፍጥ ንቅናቂ የህዋት ወያኔ ተላላኪና ርእሰ ብሄር የጦርነት አዋጅ አውጀዋል። በአየር፣በመድፍና በከባድ መሳሪያ የታገዘ የጦርነት ቃያ በጎንደር፣በጎጃም፣በወሎና በሸዋ እየነደደ ነው። ሕዝቡ የህዋት ወያኔ ትግሪዎችንና ሎሌዎችን አልይ ብሎ እየተሚሚተ ነው። ክብር ፕሮፌሰር ኮማንደር ብርሀኑ ነጋ እርሰዎ ና በእርሰዎ ፊላጭ ቀራጭነት የሚታዘዘው እሳት ራዲዮና ቴሌብዥን እንደዘገበልን ጦረዎት ከህዋት ወያኔ ሠራዊት ጋር ፊልሚያ ጀመረ ተብሎ ታሪካዊው የግንቦት ሰባት ፍሽካ ተነፋ ካሉን ድፍን ሁለት ዓመት ሞላው ።ይህ ማለት የትጥቅ ትግል ባወጁ በስድስት ዓመት ጀመሩ ማለት ነው። ለዚህም ዲያስፖራው ሳይሣሣ ለሰባት ዓመት ረድተውታል ። አሁን ግን በዚህ ፈታኝ ወቅት ክቡር ኮማንደር ብርሃኑና የጦር ሰራዊተዎ አድራሻ የውኃ ሽታ

ሁኖአል ። ብዙሀኑ ብርሀኑ ምንም ጦር የለውም ጦሩም አፍም እሳት ራዲዮና ቴሌ ብጅን ብቻና ብቻ ይሉን ነበር። እኛ ግን አላምንም ነበር። ህዝብ ውድ ሕይወቱንና ደሙን እየከፈለ እርሰዎና ድርጅተዎ እንዴት በሀገርና በትውልድ ቀልዶ በጨበጣ ውጊያና በፊዝ የሕዝብ ገንዘብ በመዝረፍ ከአስመራ ሹርቢዎች ጋር ለመደነስ ይህን ያህል የወረደ ስራ የሚሰራ ሞራል ኖሮዎት

አሁንም ሕዝባችን ለማይቀረው የድል ነፃነት ደሙን እየገበረ ከጨካኝና አረመኔ ዘረኛ ገዥዎቹ እየተፋለመ ነው። ትናንት ከብሄርተኛ ድርጅትና ቀደም ሲሉ ከህዋት ወያኔ ጋር አሁንም ከሻቢያ ጋር ለመሻረክ ዒላማና መተራረቂያ አድርገው ሲሾፍበትና ሲተርኩበት የነበረው አማራ ያለምንም ኮሽታ ህዋት ወያኔን ለመቅበር በጎበዝ አለቃ ተደራጅቶ እየተዋደቀ ነው። እርሰዎ እንደ እኛ አሰመራ ኮንቲኔታል ሆቴል ሁነው በኢንቴርኔት እየተከታተሉ ነው። ነገር ግን የንፁህን ደም አርሰዎንና መሰሎቸዎትን ይፋረዳል። አሁንም እርሰዎና ድርጅተዎ ግንቦት ሰባት በዚህ ህዝባዊ እምቢተኝነተና አመፅ ምንም አይነት አሸራ ስለላችሁ በሕዝብ ፊት የሚቆመው የውሸት መጋረጃ ስለተቀደደ በሌሎች የእንቅስቃሴ ጀርባ ለመደበቅ አልፎም አካልና ባለቤት ለመሆን የምትሟኩርት አቁሙ። ጎንደር ህብረት ባለቤቱ ብዙ ነው አይሞከር። ራሳችሁን ቻሉና ሥራችሁን አሳዩን።